ቁጥር - DFAG.F D1.9/1/26
ቀን - 06/9/2013

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለዶ/ር ሹመቴ ግዛው
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኤጀንሲውን የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን መ/ቤት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 4 ገጽ የኦዲት ሪፖርት ፤19 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ፤ 23 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች እና 1 ገጽ የመርሃ ግብር አተገባበር አባሪ በድምሩ 47 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለፅን መ/ቤቱ በግኝቶቹ ላይ የሚወስደውን የእርምት እርምጃ የሚገልፅ የድርጊት መርሃ ግብር እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ትዕግስት ሬታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ

## የ2012 በጀት ዓመት ሂሣብ

## ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት/2013 ዓ.ም

አዲስአበባ

# የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ
# የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጅ፤ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2012 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለምአቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ ( የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛና የካፒታል ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት



የፌዴራል ዋና ኦዲተር
የፋይናንስ ኦዲተር
መ/ቤት

- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፤ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፤ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

<u>የወጪ ሂሳብ፤</u>

1. በፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የውጭ አገር ነጻ ህክምና መመሪያ ቁጥር 5 መሰረት የሀገር ውስጥ ህክምና ብቻ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ኃፊዎች በየወሩ ከደመወዛቸው 1% መዋጮ መክፈል እንደሚገባቸው የተደነገገ ቢሆንም ከኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ደመወዝ ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ በድምሩ ብር 9,706.50 ገቢ ባለመደረጉ የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ እንዲቀር እና የበጀት ዓመቱ ገቢ ዝቅ እንዲል አድርጓል፡፡
2. የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ክፍያ የሚፈጽሙት ወይም ወጪ የሚያደርጉት የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን ቢገልፅም ለዲመሬጅ /ኮንቴነር በወቅቱ ባለመመለስ ለተጣለ ቅጣት/ በሚል ያለአግባብ ብር 3,879,372.34 ክፍያ በመፈፀሙ የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡
3. የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ ከመፈፀሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት ከስራ የተለዩ ሠራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር ውስጥ መውጣታቸው መረጋገጥ እንዳለበት የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቢገልፅም ኤጀንሲውን ለለቀቁ ሠራተኞች አለአግባብ ለተከፈለ ደመወዝ ብር 54,816.04 ወጪ በመደረጉ የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ ብሏል፡፡
4. የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት የሥልጠና ወጪ ብር 5,856,698.11 ተገኝቷል፡፡
5. ኤጀንሲው ከ Gates Air Inc. ለፈጸመው የዲጂታል ቴሌቪዥን ዕቃዎች ግዥ የገባው ውል የተጠናቀቀ ቢሆንም ውሉ ሳይታደስ ወይም አዲስ ውል ሳይገባ የአገልግሎት ግዜው በተጠናቀቀ ውል ብር 38,161,244.32 ክፍያ ፈፅሞ ተገኝቷል፡፡



የፌዴራል ዋና ኦዲተር
የሰነድና ግዢ
መ/ቤት

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

6. በሂሳብ መደብ 4211 ከተመለከተው ውስጥ ብር 593,148.85፤ በሂሳብ መደብ 4253 ብር 331,824.81 በድምሩ ብር 924,973.66 ተሰብሳቢ ሂሳብ ሳይወራረድ ከ5 ዓመት በላይ በመቆየቱ የበጀት ዓመቱ የተሰብሳቢ ሂሳበ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

ተከፋይ ሂሳብ፤

7. በሂሳብ መደብ 5058 ከተመለከተው ብር 19,123,821.31 ውስጥ ብር 18,856,888.66 ለገቢዎችና ጉምሩክ መተላለፍ ሲገባው ከአንድ ዓመት በላይ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ በመቆየቱ የበጀት ዓመቱ የተከፋይ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች

ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የሚቀይረው ባይሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

8. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

የመደበኛ በጀት ብር 96,151,932.11 እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 11,622,936.39 በድምሩ ብር 107,774,868.50 ሥራ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፤

ንብረት

9. የኤጀንሲው የተሽከርካሪዎች አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፡

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-13255 ፣4-13261 ፣4-13653 ፣4-21451፣ 4-13661፣ 4-13652 ፣4-13262 ለበርካታ ዓመታት፤
- የሰሌዳ ቁጥር 4-20605፤4-14097፤ 4-13649 ከ5 ወር በላይ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-13662፤4-16437፤4-13650 ከ1 ዓመት በላይ፤
- የሰሌዳ ቁጥር ፤4-20612 ከ3 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሰሌዳ ቁጥር 4-14096፤4-16965፤ 4-16961 መቼ አገልግሎት መስጠት እንዳቆሙ ያልተገለፀ፤
- የኤጀንሲው ተሽከርካሪዎች ያለአገልግሎት ካርል ሄንዝ አደባባይ በሚገኘው የኤጀንሲው ግቢ ውስጥ ቆመው ተገኝተዋል።

ከሰላምታ ጋር

ትዕግስት ረታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ**

**የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት**

**የሥራ አመራር ሪፖርት**

**መግቢያ**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የመ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

**የሪፖርቱ ዓላማ**

የዚህ ሥራ አመራር ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የኤጀንሲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁቱትና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለማስቻል ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት**

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት ኤጀንሲው ባዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ / የኦዲት አስተያየት / ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፣

- በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ የሠፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎች የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሣኔዎች መመዘን፣
- የመ/ቤቱ ሂሣብ አያያዝ የፌደራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ የተከተለ መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሂሣብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸውን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የጸዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሠራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ በመሆኑ የሂሣብ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሣይ አይችልም፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሣብ ሪፖርቶችን ኦዲት ማድረግና ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ነው፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር
የፋይናንስ ግሆዐር
መ/ቤት

የኤጀንሲው የ2012 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ፤</u>

1.1 ግኝት፤ <u>ተቀናሽ ያልተደረገ የህክምና መዋጮ ብር 9,706.50</u>

ህዳር 1999 የወጣው የፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የውጭ አገር ነጻ ህክምና መመሪያ ቁጥር 5 የሀገር ውስጥ ህክምና ብቻ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ኃላፊዎች በየወሩ ከደመወዛቸው 1% መዋጮ መክፈል እንደሚገባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የኤጀንሲው ኃላፊዎች የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ተቀናሽ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከሀምሌ1/ 2011 እስከ ሰኔ30/2012 ከዋና ዳይሬክተርና ከም/ዋና ዳይሬክተሮች በድምሩ ብር 9,706.50 በመመሪያው መሰረት ተቀናሽ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- የመንግስት መመሪያ ሊጣስ ይችላል፡፡
- መንግስት የሚያገኘውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በመመሪያው መሰረት ያልተቀነሰው የህክምና መዋጮ ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተሰጠውን አስተያየት ሙሉ በሙሉ በመውሰድ ያልተቀነሰውን ሂሳብ ተቀንሶ ለሚመለከተው ለማስተላለፍ የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን፡፡

2. <u>የወጪ ሂሳብ፤</u>

2.1 <u>ግኝት</u>፤ <u>አለ አግባብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 3,879,372.34</u>

የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6(1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ክፍያ የሚፈጽሙት ወይም ወጪ የሚያደርጉት የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን አስፍሯል፡፡ እንዲሁም በፌዴል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12 (1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት

ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የሚፈጽማቸው ክፍያዎች በመመሪያው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በቀን 05/8/2012 በሒሳብ ምዝገባ ማዘዣቁ. 0123624 ብር 1,420,162.34 እና በቀን 26/10/2012 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያቁ. 448875 ብር 2,459,209.98 በድምሩ ብር3,879,372.34 ለዲመሬጅ/ኮንቴነር በወቅቱ ባለመመለስ ለተጣለ ቅጣት/ በሚል ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

**ስጋት፤**

- ለመ/ቤቱ የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡
- ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን በብቃት ላይወጡ ይችላሉ፡፡
- አለአግባብ ክፍያ መፈፀሙ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

የመንግሥት በጀት የሚፈቀደው በእቅድ ለተያዙ ሥራዎች መሆኑንና ለቅጣት ተብሎ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ለቋሚ ዕቃ ግዥ ከተያዘ በጀት ላይ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ የመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዐትን ያልተከተለ ሆኖ በመሆኑ ሊተረም ይገባል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

ለዲሜሬጅ (ኮንቴነር) ቆይታን በተመለከተ የዲጂታል ቴሌቪዥን ፕሮጀክት እቃ የመጠባቸው ኮንቴነሮች ሲሆኑ በጊዜ እቃው ተራግፎ ወደ ሳይት ባለመሄዱ ምክንያት በተቋማችን ግቢ ውስጥ እቃውን እንደያዙ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ስለሆነ ይህም የሆነበት ምክንያት፡-

1. በሀገራችን ላይ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ፕሮጀክቱን የሚሰሩት የውጭ ድርጅቶች ሀገሪቷ ላይ ባለው ነበራዊ የጸጥታ ችግር ምክንያት ፕሮጀክቶቹ ያሉበት አብዛኞቹ ሳይቶች ከመዲናዋ አዲስ አበባ በከፍተኛ እርቀት ላይ ያሉ በመሆናቸው ፤
2. ቦታዎቹም የጸጥታ ችግር ያለባቸው መሆኑን አሁንም ቢሆን ችግሩ እየቀጠለ እንጂ እየቀነሰ ባለመሆኑ ድርጅቶቹ እቃውን አንጉዘው ፕሮጀክቱን ለመስራት ባለመቻላቸው፤
3. ለፕሮጀክቱ ስራ ከሚያስፈልጉት እቃዎች መካከል የተወሰኑት እቃዎቹን የሚያቀርበው አንዱ ድርጅት ከእንግሊዝ አገር ስለነበር የሚያቀረበው ድርጅት ውል አስሮ ለማቅረብ በሂደት ላይ እያለ የኤክስፖርት ፈቃድ የተከለከለ ስለሆነ ይህንንም ችግር ለመፍታት ግዥውን ለመፈጸም ጨረታ ካሰረው ከመንግስት ግዥ ኤጀንሲ ጋር ሰፊ ውይይት

ከተደረገ በኋላ ድርጅቱ ሌላ ሊተካው የሚችል እቃ እንዲያቀርብ ከቴክኒክ ባለሙያዎች ጋር በመወያየት መፍትሄ እስከሚሰጠው ድረስ አንዱ ድርጅት በገባው ውል መሰረት ጊዜውን ጠብቆ ስላቀረበ የቀረው እቃ እስከሚገባ መጠበቅ የግድ ይል ስለነበር፤

4. የሚሰሩት ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ሪሞት ኤሪያዎች ላይ እንደመሆናቸው መጠን ሲሰተሙ የሚገጠምባቸው የህንጻ ግምባታዎች በታሰበው ጊዜ ባለማለቃቸው ለዚህም የኮንትራክተሮች፣ የአማካሪ ድርጅቶችና የክልል መንግስታት የየራሳቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጡ በመሆኑ፤
5. እቃውን ካቀረበው ድርጅት ጋር በውላችን መሰረት የማጓጓዝ ሂደቱ በአንድ ጊዜ የማያልቅ በመሆኑ እና ሀገሪቷ ያለባትን የምንዛሬ ችግር ታሳቢ ተደርጎ ክፍያው በ4 ዙር የሚፈጸም እንዲሆን በተደረገው ስምምነት መሰረት ወቅቱን ጠብቆ የውጭ ምንዛሬ ስላልተፈቀደ በታቀደው ጊዜ እቃዎቹን ወደ ሚፈለገው ቦታ ለማጓጓዝ ለኢንስታሌሽን የሚከፈለው ገንዘብ በውጭ ምንዛሬ እጥረት በወቅቱ ስላልተከፈለ፤
6. በዝርዝር ከታየ በኋላ  እንደ ተቋም አስተዳደራዊ ውሳኔ መስጠቱ የግድ ሆኖ ስለተገኘ በኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ተወስኖ ተከፍሏል፡፡  ለዚህም ውሳኔ የተላለፈበት ኦርጂናል ደብዳቤ ከክፍያ ሰነዱ ላይ ተያይዞ ይገኛል::

ይህም የሆነበት ምክንያት ከተቋሙ አቅም በላይ በሆኑ ችግሮች እንጂ በተቋሙ የውስጥ አሰራር ድክመት ወይም ስራውን በፍጥነት ተሰርቶ እንዲጠናቀቅ ከሚደረግ የክትትል ማነስ የተፈጠረ አይደለም፡፡ ቅጣቱም እንዲከፈል የተወሰነው ከተቋሙ ቁጥጥር ውጭ መሆኑን በቅድሚያ ታይቶ  መከፈሉ እና ለህግ ተገዥ መሆን ግዴታችን ስለሆነ እንጂ የወጣው ወጪ ተቋሙን ለአላስፈላጊ ኪሳራ እንደዳረገው ሳንረዳ ቀርተን አይደለም፡፡

በቀጣይ መሰል ችግሮች እንዳይደገሙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት ሰርተን የምናሻሽለው ይሆናል፡፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

በሥራ አመራሩ በተሰጠው ምላሽ መሰረት የሚሰሩት ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ሪሞት ኤሪያዎች ላይ እንደመሆናቸው መጠን ሲሰተሙ የሚገጠምባቸው የህንጻ ግምባታዎች በታሰበው ጊዜ ባለማለቃቸው ለዚህም የኮንትራክተሮች፣ የአማካሪ ድርጅቶችና የክልል መንግስታት የየራሳቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ያልተወጡ በመሆኑ፤የሚለው ምላሽ በተቋሙ የውስጥ አሰራር ድክመት ወይም ስራውን በፍጥነት ተሰርቶ እንዲጠናቀቅ

ከሚደረግ የክትትል ማነስ የተፈጠረ አይደለም፡፡ ከሚለው ጋር ተቃረኒ ሃሳብ ነው ፡፡ስለሆነም ኤጀንሲው ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች በአግባቡ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሥራዎች በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ ሊደረግ ሲገባ በጀትን ለቅጣት ክፍያ ማዋሉ አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ እና አለአግባብ ክፍያ እንዲፈፀም ያደረጉ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል።

2.2 ግኝት፤ <u>ከሥራ ለለቀቁ የኤጀንሲው ሠራተኞች አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ ብር 54,816.04፤</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 10 ላይ የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ ከመፈፀሙ ወይም ወጪ ከመደረጉ በፊት ከስራ የተለዩ ሠራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር ውስጥ መውጣታቸው መረጋገጥ እንዳለበት ይገልፃል:: ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ ለሠራተኞች የተከፈለው የደመወዝ በመመሪያ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በኤጀንሲው በስራ ገበታቸው ላይ ከ3 ቀን እስከ 3 ወር ላልተገኙ ወይም ስራቸውን ለለቀቁ ሠራተኞች በድምሩ ብር 54,816.04 አለአግባብ የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- የመንግስት ገንዘብ ያለ አግባብ ሊወጣ ይችላል፡፡
- በኤጀንሲው ከደመወዝ ክፍያ ጋር ያለው የውስጥ ቁጥጥር ውስንነት ሊኖረው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

አላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይሰራ ተገቢው ጥንቃቄ እና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>*የሥራ አመራሩ ምላሽ*</u>

የተሰጠውን አስተያየት ሙሉ በሙሉ በመውሰድ ለቀጣይ ጥንቃቄ የምናደርግ መሆኑን እየገለጽን አባላቱም መልቀቂያ ለማስፈረም ሲመጡ ተከታትለን የምናስከፍል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

2.3 <u>ግኝት፤ የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ብር 5,856,698.11፤</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በኤጀንሲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች በዚሁ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ የሰለጠኑ ሰራተኞች የስም ዝርዝር፤ ገንዘቡ ለድርጅቶቹ ስለመከፈሉ የሚገልጽ ደረሰኝ፤ ሰልጣኞቹ ከሚሰሩበት የስራ ሂደት እንዲሰለጥኑ ጥያቄ የቀረበበት ደብዳቤ፤ ሰልጣኞቹ ከመ/ቤቱ ጋር ለስልጠናው የፈፀሙት ውል እና አሰልጣኙ አካል ሰራተኞቹ ስልጠናውን በአግባቡ እንደሰለጠኑ ያረጋገጠበት ማስረጃ ሳይቀርብ፤

- እስራኤል ሃገር በሚገኘው NamoSys በሚል ድርጅት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0123533 በቀን 30/06/12 በሂሳብ መደብ 6272 ብር 3,782,342.47 የተከፈለ መሆኑን፤
- (Avorniga Technologies Limited) ለተባለ የውጭ ድርጅት በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 448654 በቀን 14/8/2012 በሂሳብ መደብ 6272 ብር 2,074,355.64 ክፍያ መፈፀሙን፤

በድምሩ ብር 5,856,698.11 ተገቢው የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ለስልጠና በሚል ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አያስችልም::
- የመንግሥት ገንዘብ ሊባክን ይችላል፡፡

<u>ማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በመሆኑም ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ እንዲቻል ተገቢው ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ በመፈፀሙ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ሰራተኞች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት የተሟላ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ይገባዋል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

እስራኤል ሀገር ላለ ድርጅት የተከፈለ ስልጠናን በተመለከተ የሰልጣኝ ስም ዝርዝር ለሰው ሃይል ልማት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አሳውቀናል፤ ተጠቃሚው ክፍልም የሰልጣኞች

ዝርዝር አሳውቋል፣ ኦርጅናል ሰነዱ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ተያይዞ ይገኛል ክፍያውን በተመለከተ፡-

1. እንደ ተቋም ከተዘረጋው ወጥ የአሰራር ስርአት ውስጥ ለአገልግሎት ክፍያዎች ማረጋገጫ ካልቀረበ የሚከፈል ክፍያ አይኖርም ለዚህም ተጠቃሚው የስራ ክፍል አገልግሎቱን ስለማገኘቱ ማረጋገጫ (Acceptance certificate) ስልጠናውን የሰጠው ድርጅት እና ጠያቂው የስራ ክፍል በጋራ የተፈራረሙበት ማስረጃ ኦርጅናል ሰነድ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
2. ይህ የተሰጠ ስልጠና ዋነኛ አላማው የተቋሙ ተልዕኮ በቀጥታ ለማሳካት የሚሰራ ሲሰተም ስለሆነ፣ ስልጠናው የሚሰጠው በሚሰራው ፕሮጀክት ላይ የተግባር ስራ ስለሆነ በሰልጣኞቹ ቀጣይ የግል ህይወት ላይ ለመወዳደር እና ለእድገት የሚያበቃ ጉዳይ አለመሆኑን ሰልጣኞቹ በወቅቱ ተቋሙን ለሚመሩት ከፍተኛ አመራሮች ቅሬታ አቅርበው ቅሬታቸው አሳማኝ ሆኖ ስለተገኘ ውል እንዳይፈርሙ ከመግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ነገር ግን ውሳኔውን በጽሁፍ ለማድረግ በሂደት ላይ በነበርንበት ሰዓት ስራውን የሚመሩት ም/ዋና ዳይሬክተር እና ዋና ዳይሬክተር ከተቋሙ ከነበሩበት ኃለፊነት ተነስተው ወደ ሌላ ተቋም ተዘዋውረዋል፡፡
3. ገንዘቡ ስለመድረሱ ተቀባዩ ድርጅት የሰጠው ማረጋገጫ የለም ለሚለው ስጋት እንደሚታወቀው የውጭ ግዥ ሲከናወን ባንክ ለባንክ የሚደረግ ግንኙነት እንደመሆኑ መጠን ከፋዩ ድርጅት ለተከፋዩ ድርጅት እንዲከፈል ሲያዝ የተከፋዩ ድርጅት የባንክ ወኪል በአግባቡ ስለመረከቡ ሁለቱ ባንኮች ከፍተኛ ሃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፣ እስካሁን ባሳለፍናቸው የረጅም ዓመታት ልምድ ከፋይ እና ተከፋይ ብሎም የሁለቱም ወገኖች የባንክ ወኪሎች አልፎ የሚፈጸም ክፍያ ስለሆነ ተጠቃሚው ስለመረከቡ ከድርጅቱ የበለጠ የድርጅቱ የባንክ ወኪል ዋነኛ ማስረጃ ነው፡፡ ከኛ በኩል ክፍያውን ስለማስተላለፋችን ዴቢት አድቫይስ ማቅረባችን ከዚህ በፊት ከነበረን ተሞክሮ የቀጠለ እና ትክክል ነው ብለን እናምናለን፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ድርጅቶች ክፍያውን ስለመውሰዳቸው በደብዳቤ እንዲገልጹ ማድረግ ይቻላል፡፡

**<u>የኦዲተር አስተያየት</u>**

እስራኤል ሀገር ላለ ድርጅት የተከፈለ ስልጠናን በተመለከተ የሰልጣኝ ስም ዝርዝር ለሰው ሃይል ልማት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እና ተጠቃሚው ክፍልም የሰልጣኞች ዝርዝር ማሳወቁ ብቻ እንደማስረጃነት ተቀባይነት የለውም፡፣ በመሆኑም ሰልጣኞች ለሚሰለጥኑበት



የፅ/ቤት ማህተም

የስልጠና ዓይነት እና ለመ/ቤቱ የሚሰጡት አገልግሎት በውል የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም ስልጠናውን የሚሰጠው ድርጅት ሰልጣኞች ሥልጠናውን ለመውሰዳቸው እንዲሁም ለተከፈለው ክፍያም ተገቢውን ማረጋገጫ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

2.4 <u>ግኝት፤ ባልተሟላ የውል ስምምነት የተከፈለ ብር 38,161,244.32</u>

የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ታህሳስ 2003 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በክፍል 2 ቁጥር 11 ስር የካፒታል ወጪዎች ሲፈፀሙ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ማረጋገጥ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በዚህ መሰረት ኤጀንሲው በ LC ቁ. TF 1708230783 ከ Gates Air Inc. ለፈጸመው የዲጂታል ቴሌቪዥን ዕቃዎች ግዥ የካቲት 20/2008 ለ24 ወራት ስራ ላይ የሚውል ውል ተዋውሎ የግዥው ውል የካቲት 20/2010 የተጠናቀቀ ቢሆንም ውሉ ሳይታደስ ወይም አዲስ ውል ሳይገባ የአገልግሎት ግዜው የተጠናቀቀ ውል በማስረጃነት በማቅረብ በቀን 27/06/2012 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁ. 448514 ብር 38,161,244.32 ክፍያ ፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጭ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ሊወጣ ይችላል፡፡
- ተጠያቂነት ላይኖር ይችላል፡፡

<u>ማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በተሰጠው ምላሽ የቀረበው ደብዳቤ በባንክ በኩል ለተከፈተው ኤልሲ በወቅቱ ክፍያ ያልተፈጸመበትን ምክንያት የሚገልጽ እንጂ የነበረው የውል ስምምነት ጊዜው በመጠናቀቁ እንዲታደስ የተደረገበት ወይም ውሉ የተራዘመበት ባለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ለከፍተኛ የፕሮጀክት ስራዎች የሚያገለግሉ እቃዎች ግዥ ሲከናወን ከአቅራቢው ጋር የውል ስምምነት ሊፈፀም ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የዲጅታል ቴሌቪዥን ፕሮጀክት የውል ጊዜ በተመለከተ የውል ጊዜው የሚያበቃው ኤልሲ ተከፍቶ ሲዘጋ ስለሆነ በኤልሲው ጊዜ የተከናወነ ስራ ነው፡፡ በመሰረቱ ድርጅቱ ግዴታውን ተወጥቶ ስራውን አጠናቆ ለማስረከብ ከፍተኛ ጥረት ያደረገ ሲሆን አብዛኛው ችግሮች በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በተፈጠሩ ችግሮች ፕሮጀክቱ ስላልተጠናቀቅ ኤልሲው ተራዝሟል፡፡

የውል ማረዘሚያ በተመለከተ ዋነኛ አላማው በውሉ መሰረት ኤልሲውን አላራዝምም እንዳይል እና ያላቀረባቸው እቃዎች እና አገልግሎቶች ካሉ ለመጠየቅ እንዲቻል ነው፡፡ አብዛኞቹ ችግሮች ከኛ በኩል የተፈጠሩ መሆናቸውን ስለምናምን ድርጅቱ ግዴታውን ለመወጣት ወደኋላ አላለም፡፡ ምንም እንኳን ድርጅቱ ግዴታውን እየተወጣ ያለ ቢሆንም ውሉን ማራዘም ነበረብን በቀጣይ የምናስተካክለው ይሆናል፡፡

የውል ማረዘሚያ በተመለከተ ዋነኛ አላማው በውሉ መሰረት ኤልሲውን አላራዝምም እንዳይል እና ያላቀረባቸው እቃዎች እና አገልግሎቶች ካሉ ለመጠየቅ እንዲቻል ነው፡፡ አብዛኞቹ ችግሮች ከኛ በኩል የተፈጠሩ መሆናቸውን ስለምናምን ድርጅቱ ግዴታውን ለመወጣት ወደኋላ አላለም፡፡ ምንም እንኳን ድርጅቱ ግዴታውን እየተወጣ ያለ ቢሆንም ውሉን ማራዘም ነበረብን በቀጣይ የምናስተካክለው ይሆናል፡፡

## 3. ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

### 3.1 ግኝት፤ በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 924,973.66፤

በፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 4(ለ) ለስራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 4 ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ በኤጀንሲው የ2012 የበጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርት በተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ በሂሳብ መደብ 4211 ከተመለከተው ውስጥ ብር 593,148.85፤ በሂሳብ መደብ 4253 ብር 331,824.81 በድምሩ ብር 924,973.66 ከ5ዓመት በላይ ቆይታ ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

**ስጋት፤**

- ተሰብሳቢ ሂሳብ ሳይሰበሰብ (ሳይወራረድ) በቆየ ቁጥር ላይሰበሰብ የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል የመንግስት ገንዘብ ሊባክን ይችላል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

በቅድሚያ የተሰጠ ክፍያ ሳይወራረድ ተጨማሪ እንዳይሰጥ ጥንቃቄ በማድረግ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ እንዳይቆዩ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ክትትል

ሊደረግ ይገባል ፡፡ እንዲሁም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል ለቀጣይ የሚታዩ ተሰብሳቢዎችን በመቀነስ እንዲሁም ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ውሳኔ እንዲያገኙ ተገቢውን ክትትል እናደርጋለን፡፡

## 4. <u>የተከፋይ ሂሳብ፤</u>

### 4.1 <u>ግኝት</u>፤ <u>በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 18,856,888.66</u>

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መከፈሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በሂሳብ መደብ 5058 ከተመለከተው ብር 19,123,821.31 ውስጥ ብር 18,856,888.66 ከአንድ ዓመት በላይ ለገቢዎችና ጉምሩክ መተላለፍ ሲገባው ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት;</u>

- ሂሳቦቹ በወቅቱ ካልተከፈሉ የዕዳ ክምችት ሊበዛ ስለሚችል በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ በቆይታ ብዛትና በማስረጃ ዕጦት ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡
- የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ተጣርቶ መከፈል ያለበት እንዲከፈል፤ መከፈል የማይችል ከሆነ ደግሞ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከኤጀንሲው አቅም በላይ በመሆኑ ምክንያት ከገንዘብ ሚ/ር ጋር በመነጋገር በገቢዎች ኦዲት እንዲያደርግልን የተስማማን እና ሰነድ ያቀረብን ቢሆንም በገቢዎች በኩል እስከአሁን ድረስ ምንም አይነት ምላሽ ያልተሰጠን ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ያሉት የኤጀንሲው ከፍተኛ አመራሮች አዲስ ቢሆኑም ጉዳዩን በጋራ ተመልክተን ከሚመለከታቸው የገቢዎች ኃላፊዎች ጋር እና ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በውይይት በመፍታት ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን፡፡

## 5. በጀት፤

### 5.1 ግኝት፣ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 107,774,868.50፤

በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የኤጀንሲው የ2012 በጀት ዓመት የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሲደረግ፣

**የመደበኛ በጀት ብር 96,151,932.11፤**

በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከተመደበው መደበኛ በጀት ስራ ላይ ያልዋለ በድምሩ ብር 96,151,932.11 ወይም 28.10% ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**የካፒታል በጀት ብር 11,622,936.39፤**

የካፒታል በጀት ብር 11,622,936.39 ወይም 16.83% ስራ ላይ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ 3 ተመልክቷል፡፡**

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ኤጀንሲው የሚጠቀምበትን በጀት ብቻ የበጀት ጥያቄ በማቅረብ ማስፈቀድ ይገባል፡፡ በጥናት ላይ የተመሰረተ የበጀት ዝግጅት በማድረግ የሚፈቀድለትን በጀት በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

የማንጠቀምባቸውን በጀቶች ለኤጀንሲው 3 ሚስጥራዊ ግዢ እንዲውል ተወስኖ ዝውውር ተደርጎ ለሁለት ሚስጥራዊ ግዢ ኤል ሲ የተከፈተ ሲሆን ቀሪዎች በጀቶች ግን ሶስተኛውን ሚስጥራዊ ግዢ መሸፈን ስላልቻሉ ተመላሽ ተደርገዋል ዝርዝር ማብራሪያውና አስፈላጊ ማስረጃዎቹን 31 ገጽ ኮፒ ከምላሽ ማሳወቂያ ቅጹ ጋር አባሪ አያይዘናል፡፡

**የኦዲተር አስተያየት**

በሥራ አመራር ምላሹ 31 ገጽ ኮ ከምላሽ ማሳወቂያ ቅጹ ጋር አባሪ አያዘናል ለሚለው የቀረበው ማስረጃ የ2012 በጀት ዓመት መደበኛ እና የካፒታል ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ላንጠቀምበት የቻልንበት ምክንያት በሚል2 ብቻ እንዲሁም የፈሰስ ማሳወቂያ ሲሆን ለኤጀንሲው 3 ሚስጥራዊ ግዢ እንዲውል ተወስኖ ዝውውር የተደረገ ነው ለሚለው ማስረጃ አልቀረበም ፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

## 6. ንብረት፤

### 6.1 ግኝት፤ የኤጀንሲው የተሽከርካሪዎች አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፡

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 20 ከተራ ቁጥር 1-2 በተመለከተው መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑን እና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 20 ተራ ቁጥር 1 ከፊደል ሀ-መ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-13255 ፣4-13261 ፣4-13653 ፣4-21451፣ 4-13661፣ 4-13652 ፣4-13262 ለበርካታ ዓመታት፤
- የሰሌዳ ቁጥር 4-20605፤4-14097፤ 4-13649 ከ5 ወር በላይ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-13662፤4-16437፤4-13650 ከ1 ዓመት በላይ፤
- የሰሌዳ ቁጥር ፤4-20612 ከ3 ዓመት እና ከዚያ በላይ
- የሰሌዳ ቁጥር 4-14096፤4-16965፤ 4-16961 መቼ አገልግሎት መስጠት እንዳቆሙ ያልተገለፀ፤

የኤጀንሲው ተሽከርካሪዎች ያለአገልግሎት ካርል ሄንዝ አደባባይ በሚገኘው የኤጀንሲው ግቢ ውስጥ ቆመው ተገኝተዋል፡፡

**ስጋት፤**

- ከተሽከርካሪ ጋር በተያያዘ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ ሊሆን ይችላል፡፡
- የመንግሥት ንብረቶች ለብልሽት እና ለጉድለት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፤**

መጠገን ያለባቸው ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ፤ እንዲሁም መወገድ ያለባቸው በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

**የሥራ አመራሩ ምላሽ**

- 4-20612 ሞተር ላይ ችግሩ በመኖሩ ምክንያት ወደ ቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ተልከው እስካሁን መፍትሄ ያላገኘና በቅርቡ በተደረገው ተደጋጋሚ ውይይት ተፈላጊ እቃዎን ከውጪ ለማስገባት እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልፆልናል፡፡ ይህ መኪና ከተገዛ ጊዜ ጀምሮ ምንም አገልግሎት ያልሰጠ ነው ይህን ያህል ጊዜ ችግሩ ያልተፈታም በሜቴክ በኩል በነበራቸው ችግር ምክንያት ሃላፊነት ወስዶ የሚወስን ሰው ባለመኖሩ ነው፡፡
- 4-13662 ፣4-16437 ፣ 4-14097 ፣ 4-13649 እነዚህ መኪኖች የሞተር ሙሉ እድሳት የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የተወሰኑ ዕቃዎች ተገዝቶ ባለመግባታቸው እስካሁን ያልተፈታ ችግር ነው አሁንም የግዥ ሂደቱ እንዲፋጠን ከሚመለከታቸው ጋር በቅርበት እየሰራን ነው፡፡ 4-20605 በስትሪንግ ፓምፕ ብልሽት የቆመና ዕቃው በገበያ ላይ ያልተገኘበት አሁንም የዕቃ ግዥ በማፈላለግ ላይ የሚገኝ ነው፡፡
- 4-14096 ፣ 4-16965 ፣ 4-16961 ለጥገና ወደ ኢንሹራንስ የገቡና ጉዳያቸው በሂደት ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ተገቢ ጥገና ከተደረገላቸው ወደ ሥራ የሚገቡ ይሆናል፡፡
- 4-13650 ተበላሽቶ በቆመበት በመቀሌ የህግ ማስከበር ሥራ ወቅት የወደመ እና ጉዳዩ በመጣራት ሂደት ላይ ያለ መኪና ነው፡፡
- 4-13652 ኒሳን ሚኒባስ እንዲወገዱ ተወስኖ የተሸጠና የገዛው አካል የተረከበው መኪና ነው፡፡

- 4-13255 ፣ 4-13261 ፣ 4-13653 ፣ 4-21451 ፣ 4-13661 እና 4-13262 መኪኖች እንዲወገዱ ተወስኖባቸው በግዥ ኤጀንሲ በኩል ፕሮሰስ እየተደረገ ያለ ነው፡፡ እስካሁን ያልተሸጡና በሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

**በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን ::**